# የኢትዮጵያ ምጥ

ያዬ አበበ

ኢትዮጵያ ምጥ ላይ ነች። ከዚህ በፊትም ሁለቴ አርግዛ አዋላጆቿ የሚያደርጉትን ስላላወቁ እናት ብዙ ደም ፈሷት ከሞት አፋፍ ድናለች። የሦስተኛው ምጥ አዋላጅ ኢሕአዴግ ይሳካለት ይሆን?

## <u>**እንዴት እዚህ ደረስን?**</u>

በዘመናዊ ትምህርትና በምዕራባዊያንና ምስራቃዊያን ፍልስፍናና ርዕዮተ አለም  የተቀረፀው የ1960ቹ ትውልድ ኢትዮጵያን እንደሌሎቹ አገሮች የዳበረችና የበለፀገች አገር ለማድረግ ምኞቱና እምነቱ ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ፤ የንጉሱም እድሜ 80ዎቹ ውስጥ ስለነበረ፣ አለምአቀፋዊ ኢኮኖሚያዊ ሂደቶች/የነዳጅ ዋጋ ስለናረና፣ አለምአቀፋዊ ሁለት ግዙፍ የፓለቲካ ጎራዎች ገዝፈው ከመውጣታቸው ጋር ተደምሮ ኢትዮጵያን ከባህላዊ አስተዳደር ወደ ህዝባዊ አስተዳደር ተስፈንጥራ እንደትገባ የሚታገል አብዮታዊ ትግል ተጧጧፈ። አብዮትም ፈነዳ።

የተማሪው ንቅናቄ ያስተናገደውና ወደ ውስጡ ያሰረፀው የምስራቃውያን ርዕዮት ኢትዮጵያን ከኃላቀርነትና ድህነት ወደ ስልጣኔና ብልፅግና ለማሸጋገር አቻ የሌለው አማራጭ ተደርጎ በወታደሩ፣ በተማሪውና በፓለቲካ ድርጅቶች ሊሂቃን ውስጥ ቅቡልነት አገኘ። "ኢሕአዴግ ዛሬ ለምን ከአገልግሎት አሰጣጥ ተሃድሶ ይልቅ ወደ ፓለቲካዊ ስርዓት ተሃድሶ አይገባም?" ለሚለውም ጥያቄ ዋናው ምክንያቱ ርዕዮታለማዊ መሰረቱ ነው።

ኢህአዴግ በዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት የሚሰራ ድርጅት ነው። በዚህ ሌኒናዊ አወቃቀር ውስጥ ውሳኔ ከማዕከላዊ ኮሚቴ ወደ ህዝብ ይፈሳል። ከህዝብ ወደ ማዕከላዊ ኮሚቴ ውሳኔም ተፅዕኖም አይፈስም። ኢህአዴግ ይሄንን ለምን መረጠ? በተማሪው ንቅናቄ ወቅት ለኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ 'የሚመጥን' ታሪካዊ፣ ማህበረሰባዊና፣ ፓለቲካዊ ሂደት የተገኘው ከምስራቃዊያን ርዕዮተአለም ሰለነበረ ነው።

ዛሬ በኢሕአዴግና በህዝብ መካከል ያለው ቅራኔ ኢሕአዴግ ኢትዮጵያን ከሚያይበትና ከበየነበት መንገድ የተነሳ ነው። ኢሕአዴግ ኢትዮጵያ ከኃላቀርነትና ድህነት መውጣት ምትችለው በአንድ አውራ ፓርቲ አመራር ብቻ ነው ብሎ ያምናል። ይሄ እምነቱ በግልፅ የተሰመረበት ጉዳይ ነው። የአገራችን ቅራኔ እምብርቱ ይሄ መሆኑን መገንዘቡ ኢሕአዴግ የኃይል እርምጃን መንገድ ብቻ ለመምረጡ  ዋናው ማብራሪያ ነው።

የተማሪው ንቅናቄ አመራር አባል የሆነ አንድ ሰው 'በሚልየኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን መስዋዕትነንት አድርገን አገራችንን ለመለወጥ ዝግጁ ነን' የሚል ነገር እንደነገራቸው አንድ አውሮፓዊ ፀሃፊ ጠቁመዋል። ያንን

ያላቸው ሰው በ 1960ዎቹ ነው። ዛሬም ኢሕአዴግ ውስጥ ያንን አይነት ስሌት እንዳለ ከኢሕአዴግ ተግባር ማየት ይቻላል። "ህዝብ ጎርፍ ነው፣ ወደ ቀየስክለት ይፈሳል" የሚል እምነት ያላቸው ሰዎች የሚመሩት ኢሕአዴግ አገሪቱን ወደ እርስበርስ ግጭት ይዟት እየነጎደ ነው።

## <u>ወዴት እየሄድን ነው?</u>

በንጉሱም፣ በወታደራዊው መንግስትም ውስጥ የአገሪቱ አቅጣጫ ያሳሰባቸው ሰዎች አገሪቱን ከአደጋ ለመታደግ ሞክረዋል። ከነ ገርማሜ ነዋይ አንስቶ እስከነ ጄኔራል ፋንታ በላይ ድረስ ለአገሪቱ የተሻለ አማራጭ እንዳለ የተረዱ ሰዎች ራሳቸውን ለድሃው ህዝብ ጥቅም ሲሉ አደጋ ውስጥ ጨምረዋል፣ ተሰውተዋል።

ዛሬም አገሪቱ ያለችበት አደጋ ሚታያቸው ሰዎች በኢሕአድግ ውስጥ አሉ ብሎ መገመት ይቻላል። አገሪቱን ከፅንፈኛ የግራ ርዕዮት ቁማራዊ ስሌት መታደግ ከሚችሉት ውስጥ አንዱ እነዚህ ሰዎች ናቸው። መሞከርም አለባቸው። ከውስጥ የሚነሳ ለውጥ ከሌለና የኃይል እርምጃው ከቀጠለ ግን ለየት ያሉ ሰዎች ተደማጭነታቸው በህዝቡ ውስጥ እየጨመረ ይመጣል። በተለይም የመንግስትን የኃይል እርምጃ ለመቋቋምም ሆነ ለመግታትና ለማሸነፍ ተመጣጣኝ ብቻ ሳይሆን የጭካኔ ስልት መምረጥ የግድ ነው የሚለውን መስመር የሚከተሉ ታጋዮች በአገሪቱ በሰፊው ይራባሉ።

በተለይም ተጠቃሚ ናቸው ተብለው በተመደቡ ብሄሮች ላይ ብሄር ተኮር ጭካኔ እየጨመረና የትግል ስኬት መለኪያና መስፈሪያም እየሆነ ይመጣል። በክልሎች ብቻ ሳይሆን በመደናዋም ጭምር በሰፊው ግጭቱ ብሄር ተኮር ቅብ ይዞ ይስፋፋል። ይሄንን ክፍተት የሚያገኙ በሶማሌያና በኬንያ የሚገኙ አክራሪ ቡድኖች የራሳቸውን አጀንዳ ለማራመድ መንቀሳቀሳቸውም አይቀሬ ነው። አይ ኤስ ኤስም ጎራ ይል ይሆናል። በዚህ አጋጣሚም ሌሎች የጎረቤትና አካባቢያዊ አገራትም ፓለቲካዊ ስሌታቸውን ከጥቅማቸው አንፃር ያሰላሉ፣ ተፅዕኖ ማድረጋቸውንም በጣልቃገብነት በሰፊው ይያያዙታል።

እስከዛሬ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተነዛው አሉታዊ የብሄር ፕሮፓጋንዳ ፍሬ ሚያፈራውም በዚህ ወቅት ይሆናል። በተለይም በብሄር ላይ ያተኮረው 'የብሶት' ቁጣ ዱላም የሚያርፍበትን ሚያገኘውም በዚህ አጋጣሚ ነው። የኢሕአዴግ አባላትና በተለይም የስርዓቱ አራማጅ የሆኑ ግለሰቦችና ድርጅቶችን ማጥቃት የግጭቱ የሞራል ግዴታ ተደርጎ የወሰዳል። ይሄንን አይነት 'ጀብድ' ሚፈፅሙትም 'ጀግኖች' ይሆናሉ።

ይሄ ሁሉ ግን ከኢሕአድግ የርዕዮት ወንፊት/filter የተነሳ ነው። ኢሕአዴግ ከራሱ ሌላ ለአገሪቱ የሚበጅ ሃሳብ የለም ብሎ ስለሚያምንና፣ ይሄንንም እምነቱን እስከ መጨረሻው ይዞ ለመግፋት ዝግጁ ስለሆነ ነው። አገሪቱ ከብሄር ጦርነትና ከባዕዳን ጣልቃገብነት በኃላ ምን አይነት እጣፈንታ እንደሚኖራት ለመገመት አገራዊ ተሞክሮ ስለሌለን ቢያዳግትም፣ ህዝባዊ አገዛዝ እንፈጥራለን ብሎ ማሰብ ግን የዋህነት ነው። ከድጡ ወደ ማጡ

እንወርዳለን።

## **ኢሕአዴግ እንዴት ጥሩ አዋላጅ ይሁን?**

ኢሕአዴግ ብቁ አዋላጅ ለመሆን ወደ ሽግግራዊ ድርድር (negotiated transition) ከማምራት ውጪ ሌላ አማራጭ የለውም። ሽግግራዊ ድርድር ማለት የሽግግር መንግስት ማቋቋም ማለት አይደለም። ሽግግራዊ ድርድር አሁን ካለንበት የአንድ ፓርቲ የበላይነት ወደ መድብለ ፓርቲ ስርዓት ለመሸጋገር የሚያስፈልጉትን ቅድመ ሁኔታዎች የሚያመቻች ሂደት ነው። ሽግግራዊ ድርድሩ አዲስ የመንግስት ስርዓት ለመመስረት ሳይሆን ያለውን ህገመንግስታዊ አወቃቀርና ፓለቲካዊ ስርዓት ለማስተሳሰርና ወደ ህገመንግስታዊነት ሂደት ለመግባት ነው።

ሽግግራዊ ድርድር ለማድረግ ኢሕአዴግ ቢያንስ የሚከተሉትን ማድረግ ይጠበቅበታል፦

1 ኢሕአዴግ ራሱን ከአውራነት ወደ መደበኛ ፓርቲነት ደረጃ ለማውረድ መወሰን አለበት።
2 ኢሕአዴግ በፓርቲና መንግስት መካከል ልዩነት መኖር የለበትም የሚለውን አቋሙን መተው አለበት።
3 ህጋዊ ፓርቲዎች በአገር ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ የሚያቀጭጩና የሚያግዱ ህጎቹን መሻር አለበት።
4 ለሽግግራዊ ድርድር ህገመንግስታዊ መሻሻል ለማድረግ የሚያስፈልጉ ነጥቦች ላይ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለመደራደር ፈቃደኛ መሆን አለበት።
5 ለሽግግራዊ ድርድር የሚያስፈልገውን የእርቅ ሂደት ለመጀመር በመንግስታዊ የኃይል እርምጃዎች ላይ ያተኮረ የአደባባይ የምርመራ ጉባኤ ለማድረግ ፈቃደኛ መሆን አለበት።
6 ለሽግግራዊ ድርድር በቅድሚያ በአገር ውስጥ ካሉ ህገመንግስቱን ከሚቀበሉ ህጋዊ ፓርቲዎች ጋር ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ድርድር መጀመር አለበት።
7 ለሽግግራዊ ድርድር ህጋዊ ተቃዋሚዎችን እንዲያገለግሉ የህዝብ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና ጋዜጦች በቋሚነት የአገልግሎት ጊዜ መደልደል አለበት።
8 ለሽግግራዊ ድርድር በኃይል እርምጃ ውሳኔና ትዕዛዝ ላይ ከተሳተፉ ከፍተኛ አመሮች ውስጥ ከትጥቅ ትግሉ ጊዜ ጀምሮ በኢሕአዴግ ውስጥ ሲሳተፉ የነበሩ ግለሰቦች በሙሉ ከድርጅቱ በጡረታ ማሰናበት አለበት።
9 ከሽግግራዊ ድርድሮች በኃላ በአንድ ዓመት ውስጥ አገራዊና ክልላዊ ምርጫ ለማደረግ ፈቃደኛ መሆን አለበት።

ሆኖም ዛሬ ኢሕአዴግ ይሄን አይነት መንገድ ይከተላል ብሎ ማመን ግን አይቻልም።